በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA MINISTRY OF FOREIGN AFFAIRS

ፕሬስ መግለጫ PRESSRELASE

# የኳታር የሹራ ካውንስል ከኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ጋር ተቀራርቦ ለመስራት ፍላጎት እንዳለው ገለጸ

የኢፌዴሪ ልዩ መልዕክተኛና ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር መታሰቢያ ታደሰ ከኳታር የሹራ ካውንስል (Advisory Council) አፈ ጉባኤ አህመድ ቢን አብደላህ ቢን ዛይድ አል ማህሙድ ጋር ተወያዩ።



አምባሳደር መታሰቢያ የሁለቱ አገራት መሪዎች ያደረጓቸውን ይፋዊ ጉብኝቶች ተከትሎ በኳታር እና በኢትዮጵያ መካከል ያለው የፖለቲካ ግንኙነት ከመቼውም ጊዜ በላይ ከፍ ያለ ምዕራፍ ላይ መድረሱንና ይኼው ጠንካራ ግንኙነትም ለኢኮኖሚና የሕዝብ ለሕዝብ ትስስሩም በር መክፈቱን ገልፀዋል።

የፓርላማ ለፓርላማ ግንኙነትና የጉብኝት ልውውጥ መፍጠርና የሕዝብ ለሕዝብ ትስስሩን ማጠናከር ለኢኮኖሚ ግንኙነቱ መሻሻል ጥሩ መደላድል የሚፈጥር በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ አምባሳደር መታሰቢያ ተናግራዋል።

የኳታር የሹራ ካውንስል አፈ ጉባኤ አህመድ በበኩላቸው በአገራቱ መሪዎች ደረጃ የተደረጉ የጉብኝት ልውውጦች ግንኙነቱን አስተማማኝ ደረጃ ላይ እንዲደርስ አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን፣ እንዲሁም የሁለትዮሽ የኢኮኖሚ ትስስሩ እያደገ መሄዱን ገልጸዋል።

በቀጣይም በፓርላማ አባላት እና በአፈ ጉባኤዎች ደረጃ የጉብኝት ልውውጥ በማድረግ የፓርላማ ግንኙነቱ እና የሕዝብ ለሕዝብ ትስስሩ እንዲጠናከር በትኩረት እንደሚሰሩ የተከበሩ አፈ ጉባኤው አክለው ተናግረዋል።

**የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር**

**ቃል አቀባይ ጽ/ቤት**

**የካቲት 1 ቀን 2010 ዓ.ም.**

E-mail spokesperson@mfa.gov.et facebook @mfaEthspokesperson, Twitter @mfaEthspokesperson, YouTube https://www.youtube.com/channel/UCa_KUDpwCLMWyyQIjfilgZg ☎ 011-5-15 8928/011-5-53 6731 Fax 011-5-51-43-00 ✉393 Addis Ababa,Ethiopia